# ስም ማጥፋት እንደ ፖለቲካ መሳሪያ

ሳምሶን ብርሃኑ samsonbrh@gmail.com

**ታሪክ አንድ ፤ ማሌዥያ**

የማሌዥያ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የገንዘብ ሚኒስትር የነበሩት ሚ/ር አንዋር ኢብራሂም እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በሴፕቴምበር 20 ቀን 1998 ከ100ሺ ለሚበልጡ ማሌዥያውያን የሀገራቸውን አምባገነንና ሙሰኛ ጠቅላይ ሚኒስትር ማሀቲር መሀመድ ተቃውመው በኮመንዌልዝ ስብሰባ ዋዜማ ላይ ታላቅ የተቃውሞ ሰልፍ ያካሄዳሉ። አንዋር በወቅቱ በህዝባዊው ስብሰባ ላይ በሀገሪቱ የተንሰራፋውን አስከፊ ሙስናና አምባገነንነት በዝርዝር ለህዝብ አቅርበው ነበር። ህዝባዊውን ስብሰባ እንዳጠናቀቁ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ በመኖሪያ ቤታቸውም ጋዜጣዊ መግለጫ ይሰጣሉ። አንዋር መሀመድ ከዚህ አሳረኛ ቀን በፊት ጠቅላይ ሚኒስትሩን የሚተኩ እጩና ስመ ጥር ፖለቲከኛ ነበሩ። ፓራሚሊቴሪ ፖሊሶች የምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩን መኖሪያ ቤት በሮች በሰደፍ እየሰበሩ ለመግባት የጋዜጠኞችን ገለል ማለት እንኳን አልጠበቁም ።

ከዚያች ቀውጢ ቀን በኋላ አንዋር ኢብራሂም የእሳር ህይወታቸውን ሀ ብለው ጀመሩ ። ከእስር ቀናት እስር በኋላ አንዋር ወደ ፍርድ ቤት ሲቀርቡ የማሌዥያ ህዝብ የመሪያቸውንና የፖሊስ ሀይሉን ማንነት በቅጡ ነው ሊረዱ የቻሉት። አንዋር መሀመድ ፊታቸው በድብደባ ጠቁሮ እጅግ ከስተው እያነከሱ ነበር ወደ ፍርድ ቤቱ የዘለቁት ። እርሳቸው የደረሰባቸውን ሳይናገሩ ሁለት ህጻናት ልጆቻቸው ባዩት ለማንባት ጊዜ አልወሰደባቸውም ። ከሁሉም ከሁሉም ለሰሚ ግራ አጋቢው ጉዳይ የተከሰሱባቸው ባለ አስር የክስ አይነቶች ናቸው ። ከነዚሁም ውስጥ “በግብረ ሰዶም እንቅስቃሴ ይሳተፉ ነበር„ የሚለው አንዱ ነው። ለዚህም የማሌዥያ ፋሽስት መሪዎች በሀሰት የሚመሰክሩባቸው ሁሉ አዘጋጅተው ነበር። ይህም የአንዋርን ተቀባይነት ለመናድ አጥባቂ ሙስሊም ለሆነው የማሌዥያ ህዝብ ሁነኛ መላ ተደርጎ የቀረበ ስልት ነበር።

የአለም ህብረተሰብ አንዋር የተመሰረተባቸው ፓለቲካዊ ክስ ይነሳ ዘንድ ቢወተውትም ምስክሮች እንኳዋን በቅጡ ያጠኑትን ሊመሰክሩለት ያልቻሉለት የሜሌዥያ ፍርድ ቤት ግለሰቡን ወህኒ ለማውረድ ቀድሞውኑ ማስረጃ አያስፈልገውም ነበርና የአምስት አመት ፍርድ አከናንቦ ካሳሾችን ከሀፍረት ታድጓቸዋል ። ቀድሞውንም የክሱና ስም ማጥፋቱ አላማ ግለሰቡን ከፓለቲካ ማራቅ ስለነበር አንዋር የእስር ጊዜያቸን ጨርሰው ሲወጡ የፓለቲካ መብቶቻቸው ተገድቦ ነበር ።

**ታሪክ ሁለት ፣ ደቡብ አፍሪካ**

የደቡብ አፍሪካዋ ናታል ግዛት ለጥቁር ደቡብ አፍሪካዊያን ጸረ አፓርታይድ ትግል ካበረከተችው ገጸ በረከቶች አንዱ ጃኮብ ዙማ /እንደ ጎሳ መጠሪያቸው - ሚሾሎዚ / አንዱና መሪው ናቸው። በ 17 አመቱ የጸረ አፓርታይድን ትግል የተቀላቀሉት ዙማ በአፍሪካ ናሽናል ኮንግረስ / ኤ ኤን ሲ / የሃላፊነት መሰላሎች በየደረጃው ለማደግ ብዙም አልፈጀባቸውም። በአፓርታይድ ማብቂያ ላይ በቅድሚያ ወደ ደቡብ አፍሪካ ከተመለሱት የድርጅቱ መሪዎች አንዱ የነበሩት ዙማ ክሌሎቹ የድርጅቱ መሪዎች የተለየ የሚያደርጋቸው ልዩ ባህሪ ነበራቸው። ብዙም በቀለም ትምህርት ያልገፉት ዙማ ከተራው ደቡብ አፍሪካዊ ጋር መግባባቱን እጅግ የተካኑበት ነው። በዚህም ሳቢያ ያላቸው ህዝባዊ ተቀባይነት በ1999 የሀገሪቱ ምክትል ፕሬዝዳንት እንዲሆኑ አብቅቶዋቸዋል። የዙማ ህዝባዊ ተቀባይነት ማግኘት ብዙም ካላስደሰታቸው ወገኖች መሀከል የወቅቱ የደቡብ አፍሪካ ፕሬዝዳንት የሆኑት ታምቦ ምቤኪና አንዳንድ ወዳጆቻቸው ይህች ነገር ካደረች ብለው ዙማን ከፓለቲካው ጠረጴዛ ገለል የሚያደርጉበትን መላ ሲያስቡ የመጣላቸው መፍትሄ የግለሰቡን መልካም ዝና ማውደም ነበር ።

በተወሳሰቡ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች አሳሩን ለሚያየው ጥቁር ደቡብ አፍሪካዊ የመንግስትን ካዝና ከሚመዘብሩ የቀድሞ ታጋዮቹ በላይ የሚጠላው አይኖረውምና ዙማ በመንግስት ገንዘብ ያለአግባብ ማባከንና በአስገድዶ መድፈር ወንጀል ይከሰሱ ዘንድ ግድ ሆነ ። በርግጥም እነዚህን ክሶች

የሰሙ ደቡብ አፍሪካውያን የሰሙትን ማመን እስኪቸግራቸው መደንገጣቸው አልቀረም ። የስልጣን ጥም የሚያሰክራቸው አምባገነኖች ሁል ጊዜም እንደ ቁራ የሚጮሁላቸውን የመገናኛ ብዙሗን ሰዎች ከጎናቸው ለክፉ ቀን ማሰልጠናቸው አይቀርምና አንዳንድ የመገናኛ ብዙሃን ለጥቁር ደቡብ አፍሪካውያን ነጻነት የልጅነትን የጨዋታ እድሜያቸውን እንኳን የዘለሉትን የቀድሞ የትግል አጋራቸውን ጭራቅ አድርገው ለመፈረጅ ጊዜም አልወሰደባቸውም ።

በአንጻሩም የዙማ ክስ ፓለቲካዊ በቀል መሆኑን የተረዱትና ጽኑ ደጋፊዎቹ የሆኑት የሰራተኛ ማህበራት ፣ የአፍሪካ ብሄራዊ ኮንግረስ የወጣት ሊግና በርካታ የሲቪክ ተቋማት በአንድነት አቃቤ ህጉ  ክሱን እንዲያነሳ ታላላቅና ተካታታይ ሰላማዊ ሰልፎች አካሂደዋል።

ደቡብ አፍሪካ በገለልተኝነት መርህ ላይ ላነጸቻቸው ነጻ የፍትህ ተቋማት ምስጋና ይሁንና ዙማ ከቀረቡባቸው ሁሉም መሰረተ ቢስ ክሶች ነጻ ሆነው ሴፕቴምበር 2006 ነጻ ሲወጡ “በስተመጨረሽ እውነት ትዘገያለች እንጂን„ ዘምረዋል። የተፈራው የፓለቲካ ተሰሚነታቸው እውን ሆኖ ዲሴምበር 17 2007 የአፍሪካ ብሄራዊ ኮንግረስ የአመራር አባላት ምርጫ ላይ የፓርቲውን የመሪነት ቁልፍ ከከሳሻቸው ታምቦ ምቤኪ እጅ ተረክበዋል ።

## የእኛ ነገር

እንደው ለነገሩ ዛሬ ዛሬ የወገኖቻቸውን መልካም ዝና በማጉደፍ የፖለቲካና ማህበራዊ ተቀባይነት ለማግኘት ደፋ ቀና ለሚሉ ወገኖቻችን ይህን መልካም ያልሆነ ጉልድፍ ስልት እነርሱ እንዳልጀመሩት ዓለም የእነርሱን አይነት ጨዋታ እስኪታክታት እንዳየች ለማሳየት ነው ከላይ የቀረቡት መንደርደሪያ የሚሆኑ ምሳሌዎች የቀረቡት ።

እስቲ ወደ እኛው ጉድ እንግባና ወደ የት እየሄድን ነው ብለን አሁንም ራሳችንን እንጠይቅ። የዛሬ አንድና ሁለት አመት ገደማ በየእርከኑ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ከሀገራቸው ህዝብ አንገት መድፋትና ከመሪዎቻቸው እስር በላይ የሚያንገበግባቸው አሰባሳቢ ጉዳይ አልነበረም። እንዲያውም መከራ እንጂ ሀሳብ የማያሰባስበን ህዝቦች ሳንሆንም አንቀርም። ለዚህም በቂው ማስረጃ ምርጫውን ተከትሎ ህወሃት ያካሄደውን ግፍ የተመላበት ጭፍጨፋ በመቃወም የተነሱትን በመላ ምዕራብ ሀገር መዲናዎች የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ቁጥር ማስታወስ በቂ ነው ። በዋሽንግተን ዲሲ ብቻ ከ 10 እስከ 20 ሺ የሚደርሱ ኢትዮጵያውያን በታቃውሞው ሰልፍ መገኘታቸውን የአሜሪካን ድምጽ መዘገቡን የዚህ ጽሁፍ አቅራቢ ያስታውሳል ።

እነዚያ መከራቸው መከራችን ይሆን ዘንድ የተመኘንላቸው  መሪዎች እንደተፈቱ የሆነው ግን እጅግ የሚያሳዝን ነው። በፓለቲካ እንደተለመደው ወይ በስትራቴጂ አልያም እንደው ስመለከተው ድባቡ ክብድ ይለኛል አይነት ምክንያት ይሁን እስካሁን በማናውቀው መሪዎቹ ለሁለት ተከፈሉ። መለያየታቸው አስገራሚ ጉዳይ መሆኑ አብቅቷልና እርሱን አንወያይበትም። መለየቱን ተከትሎ ያስተዋልነውን የስም ማጥፋት ተግባር ግን ትንሽ ብንመክርበት አይከፋም። ይሄን ጽሁፍ ሳዘጋጅ በአንድ ድረ ገጽ ላይ እውቁን የሰብአዊ መብት ተከራካሪ የፕሮፌሰር መስፍንን የዲሞክራሲ አርበኝነት ጥያቄ ምልክት ውስጥ ሊያስገባ የታሰበ ጽሁፍ አንብቤ ይሄ ሰይጣን ኢትየጳያውያንን የተጣባው ከየት ይሆን ብዬ የስም አጥፊዎችን ፓለቲካዊና ስነ ልቦናዊ ማንነት በግሌ ለደቂቃዎች ሳሰበበት ቆየሁ ።

እስከአሁን በጥሞና የኢትዮጵያን ፖለቲካ ለተከታተለ የቅርቡን የቅንጅትም ይሁን አብዛኛዎቹን የተቀናቃኝ ፓርቲ መሪዎችን የፓለቲካ-ስትራተጂ ይሆን እንደው እንጂ በቂ የትችት ነጥብ ልናደርገው የምንችለው አንዳንዶቹን በጸረ ኢትዮጵያዊነት የተቀሩትን በወያኔነት መክሰስ እጅግ አሰቂኝ ጨዋታ ነው። ብዙዎቻችን  ንቁ የፓለቲካ ተሳትፎ እንዲኖረን እንሻለን እንጂ የተሳትፏችን ስልቱ የመሪዎችን ማንነት / ያውም በአሉባልታ ላይ ተመስርቶ / ከመጠየቅ ያለፈ አይደለም ። ምናልባት አልፎ አልፎ በአንዳንድ የፓልቶክ መድረኮችና ድረ ገጾች ብልጭ ድርግም ከሚሉ ፓለቲካዊ ጭብጥን መሰረት ካደረጉ ውይይቶች በቀር ሌላው እንዲሁ እንካ ሰላንቲያ ነው ። አንዳንዴም እንካሰላንቲያ ራሱ ብርቅ ሊሆን ይችላል - ለህሊናም ከሚከብዱት ዘለፋዎችና ስም ማጥፋቶች አንጻር ። አሁን አሁንማ ወያኔ

ተብሎ የሚፈረጀው ሰው መብዛቱ ። አንድ ሰው በአንድ ድረ ገጽ ላይ በቅርቡ አሁን ባለው አያያዝ ወያኔ ተብሎ ያልተፈረጀው ኢትዮጵያዊ ቁጥር ከእጅ ጣቶች እንደማይበልጥ በመረረ ፌዝ ገልጾት አንብቤያለሁ። በሀሳብ የተቃወመን ሁሉ ወያኔ ከሆነ ነገሩ ፖዘቲቭ አንድን በነጌቲቭ አንድ እንደመደመር ያለ ከንቱ ጨዋታ ነው። ለነገሩ አውሮፓና አሜሪካን ተቀምጠው ካፌ ላቲያቸውን እየላጡ የፌዝ ፓለቲካ እንመራለን ሲሉ የነበሩ ሁሉ ህዝብን አንቀሳቅሰው ህወሃትን እርቃኑን ያስቀሩ መሪዎችን ወያኔዎች ፣ ሀገረ ከሀዲዎች ፣ የባዕዳን ቅጥረኞች ያሉ ቀን ነው የአውሮፓና የአሜሪካንን ውሃ ጤነኛነት መጠየቅ የጀመርነው።

ተደጋግሞ እንደሚባለው የሰው ልጅን ከእንስሳት የሚለየው በማሰብ ሀይሉ ነው ። የሰው ልጅ የማሰብ ሀይሉን ካልተጠቀመበትስ ? ብሎ መጠየቅም የግድ ነው። ስም ማጥፋት የማሰብ ውጤት ሊሆን አይችልም። በእርግጥ ጤናማ ያልሆነ የማሰብ ሀይል አለ። በቅጡ ከተረዳነው ማሰብ ሊባል የማይችል አይነት። እንደ ሂትለት ውሉድ የሆነው ናዚዝም አይነት ፍልስፍና ከታመመ አዕምሮ የሚመነጭ የሀሳብ ውጤት ነው። መጨረሻው ጥፋት ብቻ ነው። ተግባሮቻችን በሙሉ በጥብቅ የተደከመበት የሀሳብ ውጤት ካልሆኑ እንዴት ብለን ነው መልካም ውጤት ሊያመጡ ይችላሉ ብለን ቀቢጸ ተስፋ ውስጥ የምንወድቀው ? የፓለቲካችን መሰረት ማሰብና መወያየት ካልሆነ እንዴት ነው ስም ማጥፋት ህወሃትን ያህል የመንግስትን ተቋማት የተቆጣጠረ ሀይል የሚያሸንፈው ? አርቲስት ደበበ በተለያዩ መድረኮች ደጋግሞ እንደጠየቀው ዘለፋና ስድብ የትኛውን የአዕምሮአችንን ክፍል ነው እንዲመራመርና እንዲጠይቅ የሚያደርገው?

ሌላው የስም ማጥፋት ፖለቲካችን አስገራሚ አካል በዚህ አጥፊ ተግባር መሪነትን የያዙት አካላት የሞራል ስፍራ ነው። በኢትዮጵያ/ ሀገር ቤት/ ስም ማጥፋት በብዛት ስላልተለመደ እዚሁ በስደት ያሉትን የፓለቲካ መሪ ተብየዎች ነው የምንመረምረው ። ዛሬ እገሌ የሲ አይ ኤ ምልምል ነው እገሌ ደግሞ ወያኔ ነው እመኑኝ የሚሉን ሰዎች እስቲ እነርሱ ላመኑበት አላማ የከፈሉትን መስዋዕትነት ይንገሩንና የተግባር ሰብዕናቸውን አይተን የሚሉትን ለመስማት እንዘጋጅ። ጸጋዬ ደብተራው ላመነበት መከራውን መብላቱ እርሱን እንድናከብረው ያደርገን እንደው እንጂ ከጎኑ ቆመው መከራውን ሊጋሩት ሲችሉ ጥለው ፈርጥጠው አውሮፓ ፊጢጥ ያሉትን የእርሱ ጀግንነት እነርሱን ያኮሰምን እንደው እንጂ ግርማ ሞገስ አያለብሳቸውም። እነዚህ ዛሬ ጸጋዬን የሚያሞካሹ ሰዎች ነገ በቅንጅት መሪዎች ላይ ካሳዩት ባህሪ አንጻር አምላክ ፈቅዶ በህይወት ቢኖርና ቢፈታ ከሁለት ስብሰባ በሁዋላ ወያኔ እንደማይሉት እንዴት እርግጠኛ መሆን ይቻላል? አንዳንዴ የማይሆን ፍልስፍና ሲበዛም ሌሎችን እንዳላዋቂ የመቁጠር ምልክትነቱ ነው ፍንትው የሚለው ። በቅርቡ አንድ የማውቀው የፓለቲካ ሰው መታሰር ጀግና አያደርግም ሲል ሰማሁና "ለአፍ ዳገት የለው" አልኩ። ታዲያ መታሰር እንዲያ ቀላል ከሆነ ብድግ ብሎ ሀገር ቤት መግባትና ለራስና ለወገን ነጻነት መታገል ነዋ። ህወሃት የባኪንግሀም ቤተ መንግስትን አልያም ነጩን ቤተ መንግስት አልተቆጣጠረ - አውሮፓና አሜሪካ ምን እናደርጋለን። ዶ/ር ብርሃኑና ዶ/ር በየነ የጥቅምቱን ታላቅ ህዝባዊ ሰልፍ ከምዕራባዊያኑ ጋር ተማክረው አከሸፉት የሚሉትም እንዲሁ የኢትዮጵያ ህዝብ ሌላ ሀገር አልሄደምና ሄደው ህዝባዊ አመጽ ይምሩና የመሪነት ክህሎታቸውን እንመልከት። እጅግ አስጨናቂና ለህይወትም ፈተና የሆኑ ፖለቲካዊ ሁኔታዎች ውስጥ ያለፉትን መሪዎች ለፖለቲካዊ ትንተናና ለትርፍ ጊዜ ማሳለፊያ መተቸት ይቻል ይሆናል ነገር ግን በተግባር ፖለቲካ እንዲያ ማድረግ እርስዎም ይሞክሩትን ያስከትላልና አደብ መግዛቱ ተገቢ ነው የሚሆነው። እንዴት ነው የሌሎች ኢትዮጵያውያንን መልካም ስምና ዝና ለማጥፋት የልብ ቁርጠኝነቱንና ድፍረቱን ያገኘነው? ከዚያም በላይ የሞራል የበላይነቱ ምን ላይ ነው የተመሰረተው ? ለዘመናት የተቃውሞ ፖለቲካዊን እየመራን ነው የሚሉን ሰዎች አንዳንድ ፓርቲዎችን "ከተመሰረቱ ስድስት ወር እንኳን ሳይሞላቸው ... አንዳንድ ወጣት የፓለቲካ መሪዎችንም "ልምድ የሌላቸው" ሲሉ የህሊና ድፍረቱን ከየት አግኝተውት ይሆን ?

**በታኝ መጣብን፣ ወያኔ መጣብን ጨኸት**

ለጽሁፌ መነሻ የሆነኝ በቅርቡ አባል በሆንኩበት የቅንጅት ስዊትዘርላንድ አንድንድ የአመራር አባላት በአንዳንድ መገናኛ ብዙሗን ያሰሙት በታኝ መጣብን ፣ ወያኔ መጣብን ኡ ኡ ታ ነው ። ነገሩ እንደ እረኛው ለቀልድ ተብሎ የተደረገ ከሆነ እውነተኛው ተኩላ የመጣ ቀን ችግር ይፈጥራልና በዚሁ ቢቀር

መልካም ነው። አለበሊዚያ ጊዜው የግልጽነትና ተጠያቂነት ዘመን ነውና እገሌ ወያኔ ነው እገሌ ደርግ ኢሰፓ ነው ወጣት ሲረሽን የኖረ ብሎ ጨዋታ በዘመነ ቴክኖሎጂ ብዙም አይበጅም ።

ኢትዮጵያ ዘላቂ የሆነ ፖለቲካዊም ይሁን ሁለንተናዊ የማህበረሰብ ለውጥ ታመጣ ዘንድ በየትኛውም ስፍራ ጠያቂ ትውልድ መፍጠር ነው የጊዜው ፍልስፍና። ማናቸውም የፖለቲካ ይሁን ማህበረሰባዊ አቋሞች ከመያዛቸው በፊት መመራመርና መወያየት ብቻ ነው ከድንቁርና የሚያወጣን። “ሁሉም እንስሳት እኩል ናቸው አንዳንድ እንስሳት ግን የበለጠ እኩል ናቸው„ ስብከት ቢያንስ ቢያንስ ዛሬ አጅግም አይሰራም። ካላይ እንዳነሳናቸው ታሪኮች የግለሰቦች ማንነት በጊዜ ነጥሮ መውጣቱ አይቀርም። በሃሳብ የተቃወመህን ኦ ነ ግ ፣ ገንጣይ ብሎ ጨዋታ መጨረሻ ላይ የእራስን መገንጠል ያመጣል። የፖለቲካ አመራር እንስጣችሁ የመሪነቱም ችሎታ አለን የሚሉ ሁሉ አንድ ልብ ሊሉት የሚገባ እውነት አለ። መሪነት በህዝብ ውስጥ የሚፈጠር ስሜት ነው ፣ የህዝብ እምነት እንጂ ለራስ የሚሰጡት ክህነት አይደለም። ህዝብን ማድመጥ፣ የህዝብን ፍላጎት መረዳት ግድ ነው። ህዝብ አያውቅም ሬድዮኑም ቴሌቪዥኑም የእኔ ነው ብሎ ፕሮፓጋንዳ ለመጋት መሞከር እነ መለስም ዘንድ ያየነው ነውና አዲስ ስለማይሆንብን አያደናግረንም ።

የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ታምራት ላይኔ ብዙ አጥፊ ተግባራትን ቤተ መንግስት ሲሰሩ ከርመው ወህኒ ቤት ከገቡ ነው አንድ ታላቅ ፍልስፍና የሚሆን እውነት የተናገሩት። ግለሰቡ በአቶ ስየ አብርሃ ላይ በሀሰት ከመሰከሩ የተፈረደባቸው የ16 አመት እስራቸው በይግባኝ እንደሚቀነስላቸው በህወሃት ሲወተወቱ “ተውኝ ስህተትን በስህተት አላርምም„ ነው ያሉት። በወቀቱ መለስን ተከትለው ያጠፉት ሁሉ ወለል ብሎ ታይቷቸው ይሆናል። እኛም እስከዛሬ የተሳሳትነው ቢያበቃ ነው የሚሻለው። ውሸትና ስም ማጥፋት የየትኛውንም ቡድን ጥቅሞች ለዘለቄታው አስጠብቆ አያውቅም። የምንሟገት ከሆነ ቁም ነገሩ ላይ እንጂ እኔ ከዚህኛው ከወርቁ አንተ ከጨርቁ አይነት አይረቤ ጭቅጭቅ በይበልጥ ማንነታችንን ፈተና ውስጥ ነው የሚጥለው። ዛሬ ኢትዮጵያውያን ለመለስ ቅልብ አጋዐዚ ጦርም አንገት አልደፋም - እንኳን በባዕድ ሀገር ለሚደረግ ስም ማጥፋትና ጥላሸት መቀባት። የሚያበቃ ከሆነ እዚህ ላይ ያብቃ ፡/እረ አይበቃም ወይ ነው ያለው ከያኒው ?/ ስም መጠፋፋቱን አቁመን ዋናውን ዲሞክራሲን በሀገራችን የመትከል ትግላችንን በጋራ እንሞክረው።

**እግዜያብሄር ኢትዮጵያን ይባርክ**

ፌብሩዋሪ 2008